# በአየርላንድ የኢትዮጵያውያን ማኅበር

# ሁለተኛ ተሻሽሎ የቀረበ

# ሕገ ደንብ

# ነሐሴ 2011 ዓ/ም (August 2019)

## መግቢያ

በአየርላንድ የምንኖር ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከትውልድ አገራችን ርቀን በመኖር የሚያጋጥሙንን የተለያዩ ችግሮች በጋራ ለመቅረፍና አገራችን ኢትዮጵያንም ለማስተዋወቅ በአየርላንድ የኢትዮጵያ ማህበር ተቋቁሟል።ማህበሩ ከምንኖርበት አገር ባህል ህግና የኑሮ ዘይቤ ጋር በማጣጣምና ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ የሚያግዘን ሲሆን ከማንኛውም የዘር፤የፖለቲካና የሃይማኖት ዓላማ የጸዳ ነው።አገራችን ኢትዮጵያ እንደማንኛውም ሌሎች አገሮች በተለያዩ ቋንቋዎችና ባህሎች የበለጸገች ናት። አገራችን በታሪክ በዓለም ላይ ካሉት ቀደም ያለ ታሪክ ካላቸው አገሮች ውስጥ የምትሰለፍ በመሆኗና፤ ይህንንም  የማስተዋወቅና የመጠበቅ የውዴታ ግዴታም ስላለብን ይህ ማህበር ተመስርቷል።

## አንቀጽ 1 ስያሜ

**1-1 የማህበሩ መጠሪያ የኢትዮጵያውያን ማህበር በአየርላንድ ተብሎ ይጠራል።**

## አንቀጽ 2 የደንቡ ተፈጻሚነት ወሰን

**2-1 ይህ የኢትዮጵያውያን ማህበር ሕገ ደንብ በመላ አየርላንድ በሚኖሩ የማህበር አባላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።**

## አንቀጽ 3 አድራሻ

**3-1 የማህበሩ ዋና ጽህፈት ቤት በአየርላንድ ዋና ከተማ በደብሊን ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ከተሞች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሊኖረው ይችላል።**

## አንቀጽ 4 የማህበሩ ዓላማ

**4-1 የመተሳሰብ የመተባበርና በፍቅር አብሮ የመኖርን ባህል ለማዳበር እንዲሁም በግል ወይም በጋራ የሚያጋጥመንን ችግሮች በጋራ ለመቋቋም እንድንችል፤**

**4-2 በሞት፤በህመም፤በአደጋ፤በስራ ማጣት ወዘተ የኢኮኖሚ ችግር ለሚያጋጥማቸው የማህበረሰቡ አባላት ምክር ድጋፍና  ዕርዳታ ለማድረግ፤**

**4-3 በአየርላንድ የሚኖሩና አዲስ የሚመጡ ኢትዮጵያውያንን በኢኮኖሚ፤ በማህበራዊ ኑሮ ፤ በስራ፤በትምህርትና በሌሎች ጠቃሚ መስኮች የሚረዱበትን መንገድ እያጠና ተግባራዊ ለማድረግ፤**

**4-4 የኢትዮጵያን የተለያዩ ባህሎች፤ ወጎችና ቅርሶችን ለማስተዋወቅና ለመጠበቅ፤**

**4-5 ከኢትዮጵያውያን ወላጆች የተወለዱ ልጆችና በማደጎ ወደ አየርላንድ መጥተው የሚኖሩ ህጻናት አገራቸውን ኢትዮጵያን እንዲያውቁ፤እንዲያፈቅሩ፤ቋንቋቸውና ባህላቸውን እንዲያስታውሱ እንዲማሩና እንዲያዳብ፤**

**4-6 በአየርላንድ ካሉ ተመሳሳይ ይዘትና ዓላማ ካላቸው ሌሎች ማህበራትና ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ኢትዮጵያውያን ልምድ እንዲለዋወጡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።**

## <u>አንቀጽ 5 የአባልነት መስፈርቶች</u>

**የማህበሩ አባል ለመሆን ከዚህ በታች የተጠቀሱትን የሚያሟላ መሆን ይችላል።**

**5-1 በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች**

**5-2 ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ፤**

**5-3 የማህበሩን መተዳደሪያ ሕገ ደንብ የተቀበለ፤**

**5-4 በአየርላንድ ነዋሪ የሆነ።**

## <u>አንቀጽ 6 የክብር አባልነት</u>

**6-1 በአንቀጽ 5 ላይ የተጠቀሰውን የማያሟሉ ሆነው ነገር ግን ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያውያን ጋር የቅርብ ግንኙነት ያላቸውና የማህበሩን ህጎችና ደንቦች የተቀበሉ የክብር አባል መሆን ይችላሉ፤**

**6-2 የማህበሩ የክብር አባል የሆነ በደብዳቤ ጥሪ ካልተደረገለት በስተቀር በማህበሩ ጠቅላላ ስብሰባ ላይ መገኘት አይችልም፤**

**6-3 የማህበሩ የክብር አባል ከማህበሩ ቦርድ ጋር በመነጋገር ለማህበሩ የተለያዩ እገዛዎችን ማድረግ ይችላሉ።**

## <u>አንቀጽ 7 የአባልነት ግዴታዎች</u>

**7-1 ማንኛውም አባል ማህበሩ የሚወስናቸውን ውሳኔዎች ተግባራዊ ማድረግ አለበት፤**

7-2 ማንኛውም አባል የማህበሩን ህግና ደንብ የማክበር፤የመጠበቅ ዓላማዎቹንና የመፈጸምና የማስፈጸም ሃላፊነት አለበት፤

7-3 ማንኛውም አባል ማህበሩ በሚጠይቀው የስራ ድርሻ መሳተፍ አለበት፤

7-4 ማንኛውም አባል የመምረጥም ሆነ የመመረጥ ሃላፊነት አለበት፤

7-6 በአባላት መካከል የመግባባትና የመተባበር ስሜት እንዲዳብር ምሳሌ የመሆን አለበት፤

7-7 ማንኛውም አባል በጠቅላላ ጉባኤ መሳተፍ ይጠበቅበታል፤

7- 8 ማንኛውም አባል የአባልነት ክፍያ መፈጸም ይጠበቅበታል።

## አንቀጽ 8 የአባላት ጥቅሞች

8-1 እያንዳንዱ አባል ከማህበሩ የሚገኝን ማንኛውም ጥቅም በእኩልነት የመካፈል መብት አለው፤

8-2 የማህበሩ አባላት ማህበሩ በሚያካሂዳቸው እንቅስቃሴዎች ውስጥ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ የሚያስገኙ የተለያዩ ስራዎች በሚፈጠሩ ጊዜ አባላት መሳተፍ ይችላሉ።ስራውን ለማግኘት ከአንድ በላይ አመልካቾች ከቀረበ ግን ቦርዱ ከተወዳዳሪዎቹ ጋር ግልጽ ውይይት በማድረግ ወይም በማወዳደር ይወስናል፤

8 -3 ማንኛውም አባል ጋብቻ ሲፈጽም ለአንድ ጊዜ የ የ250 /ሁለት መቶ  ሃምሳ/ ዩሮ ስጦታ ያደርጋል።የማህበሩ አባላት የሆኑ እርስ በርስ ጋብቻ ቢፈጽሙ ክፍያ የሚደረገው እንደ አንድ አባል ተደርገው ነው፤

8-4 የማህበረሰቡ አባል በሞት ከተለየ ለተጠሪው አካል 1000/አንድ ሺ/ ዩሮ ይሰጣል፤

8 -5 ከአባል ጋር አብረው በሚኖሩ ቤተሰብ የሞት አደጋ ቢደርስ ለወጪ መሸፈኛ 500 /አምስት መቶ/ ዩሮ ይሰጣል።እንዲሁም እዛው ቤተሰብ ውስጥ በእንግድነት የመጣ ቢኖርና የሞት አደጋ ቢደርስበት ክፍያው እንደ አንድ ቤተሰብ ተቆጥሮ 500/አምስት መቶ/ዩሮ ይሆናል፤

8-6 በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ከሁለትና ከሁለት በላይ የማህበር አባል ቢኖር ክፍያ የሚደረገው አንድ ጊዜ ብቻ ነው።

8-7 ማንኛውም የጋብቻ ወይም የሃዘን ክፍያ የሚፈጸመው ማህበሩ ከተመሰረተ ከአንድ ዓመት በኋላ ሆኖ፤ ወጪ የሚያስፈልገው ሁኔታ ሲያጋጥም በማንኛውም ጊዜ ይፈጽማል፤

8-8 ማህበረሰቡ አባል አባልነቱን የሚገልጽ ደብዳቤ እንዲጻፍለት የፈለገ እንደሆነ መብትና ግዴታዎቹን በአግባቡ የፈጸመ መሆኑን ተመልክቶ የጠየቀውን ይፈጽምለታል።

## አንቀጽ 9 የአባልነት ክፍያ

**9-1 የማህበሩ የአባልነት ክፍያ በግለሰብ በወር 5/ አምስት/ ዩሮ ነው፤**

**9-2 ማህበሩ ከተመሰረተ ከአንድ ዓመት በኋላ አዲስ የሚገቡ የማህበሩ የአባልነት ክፍያ ለመመዝገቢያ 20/ሃያ/ ዩሮ ይሆንና በተጨማሪም ወርሃዊውን ክፍያ 5 /አምስት/ ዩሮ ይከፍላል፤**

**9-3 ማንኛውም ነባር አባል ሆነ አዲስ ገቢ ተጨማሪ ገንዘብ መክፈል ይችላል።**

## አንቀጽ 10 ከማህበረሰቡ ስለመሰናበት

**10-1 ማንኛውም የማህበረሰብ አባል በማንኛውም ጊዜ በራሱ ፈቃድ የማህበረሰብ አባልነቱን ማቆም ይችላል። ከማህበረሰቡም የሚለቅበትን ምክንያት ገልጾ ደብዳቤ ሲጽፍ ከማህበረሰቡ የምስክር ወረቀት ማግኘት ይችላል፤**

**10-2 የአባልነት ክፍያን ለአንድ አመት ያልከፈለ ግዴታውን እንዳልተወጣ ተነግሮት ይሰናበታል፤**

**10-3 አየርላንድን በቋሚነት መሄዱን በጽሁፍ ሲያሳውቅ በደብዳቤ ይሰናበታል፤**

**10-4 ከማህበረሰቡ የለቀቀ አባል ለአባልነት የከፈለው ገንዘብ አይመለስለትም።**

## አንቀጽ 11 ከማህበሩ የሚያሰናብቱ አስገዳጅ ሁኔታዎች

**11-1 ከማህበረሰቡ ዓላማዎች ውጪ ማህበሩን የሚጎዳና የሚያዳክም ፤**

**11-2 በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ አባላትንና የአባላትን ጥቅም የሚጎዳ ድርጊት የሚፈጽም፤**

**11 -3 ስለ ማህበሩ አሉባልታ የሚነዛ፤ቡድንተኛ የሆነ፤የመበተንና ከፋፋይ ወሬዎችን የሚያወራ፤**

**11-4 ከማህበረሰቡ ዓላማ በተቃራኒ የቆመ፤**

**11-5 የአባልነት ግዴታዎችን ማከናወን ከተሳነውና ለሌሎች መጥፎ አርአያ ከሆነ ከማህበሩ ይሰናበታል።**

## አንቀጽ 12 ወደ ማህበሩ ተመልሶ ስለ መግባት

**12-1 ከማህበሩ አባልነት የለቀቀ ወደ ማህበሩ በማንኞውም ጊዜ እንደ አዲስ አባል በጽሁፍ አመልክቶ እና ቅጣት ሰላሳ /30/ ዩሮ ከፍሎ ተመልሶ መግባት ይችላል፤**

12-2 ከማህበሩ የተሰናበተው በዲስፒሊን ጥፋት ከሆነ የሚጽፈው ደብዳቤ ይቅርታ እንዲደረግለት የሚገልጽ መሆን

አለበት፤

12-3 ለሁለተኛ ጊዜ ከማህበሩ በዲስፒሊን ከተሰናበተ በምንም መንገድ ወደ ማህበበሩ መመለስ አይችልም።

## አንቀጽ 13 የገቢ ምንጮች

13-1 ከአባልነት የሚገኝ መመዝገቢያና ወርሃዊ መዋጮ፤

13-2 የተለያዩ ገቢ ማግኛ መንገዶችን በመፈለግ፤ ዝግጅቶችን በማቅረብ፤ ዓመታዊ በዓላትን በማክበር፤

13-3 የፕሮጀክት ሃሳቦችን በመቅረጽና የተለያዩ ድርጅቶችን ዕርዳታ በመጠየቅ፤

## አንቀጽ 14 ጠቅላላ ጉባዔ

14-1 የኢትዮጵያውያን ማህበር በአየርላንድ ዓላማ ለማራመድ የአባልነት ግዴታዎችን የሚወጡ አባላትን በሙሉ ያካተተ ስብስብ ነው፤

14-2 ወሳኝ የሆኑና በደንቡ ላይ የተመለከቱትን የማህበሩን ጉዳዮች የመወሰኛ የመጨረሻው አካል ነው።

14-3 የስራ አስፈጻሚ አባላትንና የቦርድ አባላትን ይመርጣል፤

14-4 ከየኮሚቴዎቹ የሚቀርቡለትን የስራ አፈጻጸምና የኦዲት ሪፖርቶች አዳምጦ ውሳኔ ያሳልፋል፤

14-5 የቦርዱ ሰብሳቢ ጠቅላላ ጉባዔ ከጠራ ይሰበሰባል፤

14-6የተጓደሉ የስራ ቦታዎች ካሉ በምትኩ ሌላ ይመርጣል፤

14-7 ዓመታዊ በጀት ያጸድቃል፤አፈጻጸሙም ህግና ደንብ የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል፤

14-8 የመተዳደሪያ ደንቡን ያጸድቃል፤እንዳስፈላጊነቱ በቦርዱ ተሻሽሎ ሲቀርብ ያጸድቃል፤

14-9 ከማህበሩ አባላት ከግማሽ በላይ ከሆነ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤

14-10 ምልዓተ ጉባዔ በመጀመሪያው ስብሰባ ላይ ካልተገኘ በሁለተኛው ስብሰባ በዕለቱ ከተገኙት ከ 75% በላይ ስብሰባ እንዲቀጥል ከተስማሙ ጉባዔውን ማካሄድ ይችላሉ።

## አንቀጽ 15 ቦርድ

**15-1 ቦርዱ በጠቅላላው ጉባኤ የተመረጡ አምስት አባላት ይኖሩታል፤**

**15-2 የቦርዱ ሰብሳቢ በቦርዱ አባላት የሚመረጥ ይሆናል፤**

**15-3 የስራ አስፈጻሚው ሰብሳቢ የቦርዱ ጸሃፊ ይሆናል፤**

**15-4 በጠቅላላ ጉባዔው ከሚመረጡት የቦርድ አባላት ውስጥ ሁለቱ በየሶስት ዓመቱ በአዲስ ይተካሉ።**

## <u>አንቀጽ 16 የቦርዱ ተግባር</u>

**16-1 ለጠቅላላ ጉባዔው ተጠሪ በመሆን ማህበሩ የተቋቋመለትን ዓላማና ተግባር ከግብ ለማድረስ ኃላፊነት የተሰጠው የማህበሩ የበላይ ጠባቂና አስተዳዳሪ ወይም መሪ አካል ነው፤**

**16-2 የማህበሩ ህጎችና ደንቦች በስራ አስፈጻሚው በትክክል መተርጎማቸውንና መፈጸማቸውን በበላይነት ይቆጣጠራል፤**

**16-3 ስራቸውን በብቃት ለመወጣት ያልቻሉ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ጉዳይ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ጉዳዩን ለጠቅላላ ጉባዔ አቅርቦ ያስወስናል፤**

**16-4 የማህበሩ የመተዳደሪያ ደንቦች እንዲሁም ዓላማዎቹ እንዲዳብሩና ጥልቀት እንዲያገኙ አዳዲስ የማሻሻያ ሃሳቦችን እያጠና ለጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፤**

**16-5 ስራ አስፈጻሚው ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ግለሰቦች፤ማህበራትና ድርጅቶች ጋር የሚፈጥረው ግንኙነት ከዘር፤ከፆታ፤ ከሃይማኖትና ከፖለቲካ ነጻ መሆኑን ይቆጣጠራል፤**

**16-6 በማህበሩ ውስጥ የሚከሰቱ ማንኛውንም አለመግባባቶች የስልጣን ተዋረዱን ጠብቆ ሲቀርብለት የማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብና መንፈስ በመመርኮዝ መፍትሄና መመሪያ ይሰጣል፤**

**16-7 የማህበሩን ዓርማ ወይም መታወቂያዎች ፤ፎርሞች፤ቅጾችና የስራ ሰነዶች /ለምሳሌ መጽሄቶች፤ድረ ገጾች / ስሞች የማህበሩን ሁለንተናዊነት የሚያንጸባርቁ እንዲሆኑና ተጠንተው እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤**

**16-8 በስራ አስፈጻሚው የሚቀርበውን አጠቃላይ የስራ ሪፖርት ተመልክቶ ለጠቅላላ ጉባዔው እንዲቀርብ ያደርጋል፤**

**16-9 በየሶስት ወሩ በመሰብሰብ የማህበሩን የስራ አስፈጻሚ እንቅስቃሴ ከስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያደምጣል፤እርማት ይሰጣል፤ያጸድቃል።**

## <u>አንቀጽ 17 የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ</u>

17-1 ዘጠኝ አባላት ያሉት የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባዔ ይመረጣል፤

17-2 ከስራ አስፈጻሚ አባላት ውስጥ አራቱ በየሶስት ዓመቱ በአዲስ ይተካሉ፤

17-3 ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔውና ለቦርዱ ይሆናል፤

17-4 የማህበረሰቡን የዕለት በዕለት ስራ ይመራል፤

17-5 የማህበረሰቡን ዓመታዊ ዕቅድና በጀት አውጥቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤ሲጸድቅለትም ስራ ላይ ያውላል፤

17-6 እንደ አስፈላጊነቱ ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያዋቅራል ፤ምክንያቱንም ገልጾ ለቦርዱ ደብዳቤ ይጽፋል፤

17-7 ፕሬዝዳንት ፤ምክትል ፕሬዝዳንት ፤ጸሃፊ፤ ገንዘብ ያዥ፤ ሂሳብ ሹም፤የውስጥ ኦዲተር፤ የህዝብ ግንኙነት፤የባህልና ስፖርት፤ሴቶች ወጣቶችና ህጻናትን የሚወክሉ ንዑስ ኮሚቴዎች ይኖሩታል።

## አንቀጽ 18 ፕሬዝዳንት

18-1 በስራ አስፈጻሚው ኮሚቴው አባላት ይመረጣል፤

18-2 የቦርዱ ጸሃፊ ሆኖ ያገለግላል፤

18-3 የማህበሩን የዕለት በዕለት ስራ ይመራል፤

18-4 ከቦርዱ የጸደቀለትን ዓመታዊ ዕቅድና በጀትያስፈጽማል፤

18-5 ሂሳብ ሹሙ ከፕሬዝዳንቱ ወይም ከምክትል ፕሬዝዳንቱ ጋር በመሆን ቼክ ላይ ይፈርማል፤

18-6 ለማህበሩ ለሚጻፉ ደብዳቤዎች መልስ ይጽፋል፤በየሶስት ወሩ ለቦርዱ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ያቀርባል፤

18-7 ስራቸውን በትክክልና በብቃት መወጣት ላልቻሉ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ሲኖሩ ለቦርዱ በማቅረብ አስፈላጊውን ውሳኔ ያስወስናል፤

18-8 የማህበሩ ፕሬዝዳንት በሚመራው ስብሰባ በድምጽ አሰጣጥ ጊዜ ሁለት ድምጽ ይኖረዋል።

## አንቀጽ 19 ም/ ፕሬዝዳንት

19-1 በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ይመረጣል፤

**19-2 የማህበሩ ፕሬዝዳንት በሌለበት ወቅት ፕሬዝዳንቱን በመተካት ከላይ በአንቀጽ 18 የተጠቀሱትን ያከናውናል፤**

**19-3 ፕሬዝዳንቱ በችግር ወይም በሌላ ምክንያት ስራውን መቀጠል ባይችል ጠቅላላ ጉባዔ ተጠርቶ ተተኪ እስኪመረጥ ድረስ የስራ አስፈጻሚውን ኮሚቴ ይመራል፤የቦርዱ ጸሃፊም ሆኖ ያገለግላል፤**

**19-4 በስራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ስር የሚዋቀሩትን ንዑሳን ኮሚቴዎች ይመራል።**

## <u>አንቀጽ 20 ጸሃፊ</u>

**20-1 የስራ አስፈጻሚውን ኮሚቴ ስብሰባ አጀንዳዎች ከፕሬዝዳንቱ ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፤የስብሰባ ቃለ ጉባዔ ይይዛል፤ የስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋል፤**

**20-2 የማህበሩን ዶክመንቶችንና ማህተሞችን ይይዛል፤**

**20-3 የማህበሩን የዕለት በዕለት የጽህፈት ስራ ይመራል፤ለማህበሩ የተላኩ ደብዳቤዎች ወቅታዊ ምላሽ እንዲያገኙ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል፤**

**20-4 ከስራ አስፈጻሚው የተወሰኑትን ውሳኔዎች ለአባላት ያስተላልፋል፤**

**20-5 ፕሬዝዳንቱና ምክትል ፕሬዝዳንቱ በሌሉበት ጊዜ የስራ አስፈጻሚውን ስብሰባ ይመራል፤ ፕሬዝዳንቱና ምክትል ፕሬዝዳንቱ ስራቸውን መቀጠል ባይችሉ ጠቅላላ ጉባዔ ተጠርቶ ተተኪዎች እስኪመረጡ ድረስ የስራ አስፈጻሚውን ኮሚቴ ስራ ይመራል፤**

**20-6 የአባላትን የስም ዝርዝርና ወቅታዊ የሆነ ሙሉ መረጃ ይይዛል።አባላትን የተመለከተ የግል መረጃዎች ከጉዳዩ ባለቤት ውጪ ያለፈቃዳቸው በምንም መንገድ ከማህበሩ ውጪ ላሉ ግለሰቦች እንዳይደርስ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋል።**

## <u>አንቀጽ 21 ሂሳብ ሹም</u>

**21-1 ከስራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ጋር በመመካከር የማህበሩን በጀት ያዘጋጃል፤በንዑሳን ኮሚቴዎች የሚቀርቡለትን ዓመታዊ በጀቶች ከአጠቃላይ የማህበሩን በጀት ጋር ያመሳክራል፤ ከፕሬዝዳንቱ ጋር በመሆን የማህበሩን አጠቃላይ በጀት ለቦርዱ ያቀርባል፤**

**21-2 በቦርዱ የጸደቀው በጀት በትክክል ስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤**

**21-3 ከገንዘብ ያዢ/ ንብረት ሃላፊና ከውስጥ ኦዲት ኮሚቴ ጋር በመሆን የማህበረሰቡን የሂሳብና የንብረት ቅጾች ያዘጋጃል፤**

**21-4 ከገንዘብ ያዢ/ ንብረት ሃላፊ / የወጪ ዝርዝሮችን ወቅታዊ በሆነ መንገድ በመሰብሰብ የገቢና ወጪ ዘገባን በየስድስት ወሩ በማዘጋጀት ለስራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ያቀርባል፤**

**21-5 የማህበሩን የታክስ ፋይል ያዘጋጃል፤**

**21-6 ከፕሬዝዳንቱ ወይም ከምክትል ፕሬዝዳንቱ ጋር በመሆን ቼክ ላይ ይፈርማል።**

## አንቀጽ 22 ገንዘብ ያዥ/ንብረት ሃላፊ/

**22 -1 በዘመናዊ የገንዘብና የንብረት አያያዝ ዘዴ የማህበሩን ገንዘብ፤ንብረት ይይዛል፤ ይቆጣጠራል።ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ተገቢውን እንክብካቤ እንዲያገኙ ያደርጋል፤**

**22-2 የአባልነት መመዝገቢያና ዓመታዊ ክፍያን ይሰበስባል፤ህጋዊ ደረሰኝም ይሰጣል፤**

**22-3 ማንኛውም ገቢና ወጪ ሃላፊነትና ስልጣን በተሰጠው አካል አማካኝነት እንዲፈጸም ያደርጋል፤**

**22-4 የማህበሩን ቼክ ይይዛል፤**

**22-5 ለዕለት ተዕለት ተግባሮች የሚያስፈልጉትን የጽህፈትና ሌሎች ቁሳቁሶች ያቀርባል፤ ይቆጣጠራል፤ለጥቃቅን ወጪዎች የሚሆን ገንዘብ ይይዛል፤**

**22 -6 ለእያንዳንዱ ወጪና ገቢ ደረሰኝ ግልባጩን ለሂሳብ ሹሙ ያስረክባል።**

## አንቀጽ 23 የውስጥ ኦዲተር

**23-1 የማህበሩን የገንዘብ የሂሳብና የንብረት አያያዝ ደንብ በማዘጋጀት በቦርዱ ሲጸድቅ ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ያስተላልፋል፤**

**23-2 በአመት አንድ ጊዜ ዝርዝር የኦዲት ሪፖርት ለቦርዱ፤ለስራ አስፈጻሚውና ለጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፤**

**23-3 እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም የስራ ጊዜ የገንዘብ ሆነ የስራ አፈጻጸም ምርመራና ኦዲት በማድረግ ለቦርዱ ወይም ለጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፤**

**23-4 የስራ ዘመን ከመጠናቀቁ ከ2 ወር በፊት ዝርዝር የኦዲት ሪፖርት ያዘጋጃል፤የርክክብ ሰነድ በማዘጋጀት አዲስ ተመራጮችና ነባሮች እንዲፈራረሙ ያደርጋል።**

## አንቀጽ 24 ህዝብ ግንኙነት

**24-1 የማህበሩን ዓላማና የስራ እንቅስቃሴ ለመገናኛ ብዙሃን ያሰራጫል፤**

**24-2 የማህበሩንን ድረ ገጽ፤ ፌስ ቡክ፤ትዊተር ወዘተ ያስተዳድራል፤ወቅታዊ መረጃዎችን ያስቀምጣል፤**

**24-3 የጠቅላላ ጉባዔውን ፤የቦርዱን፤የስራ አስፈጻሚውን ስብሰባ በቪድዮ በመቅረጽ ፋይል ያደርጋል፤**

24-4 ዓብይ የስራ እንቅስቃሴዎች በድምጽና በምስል በመቅረጽ ለህብረተሰቡ ያደርሳል፤

24-5 የማህበሩን እንቅስቃሴ የሚያሳይ መጽሄት ወይም በራሪ ወረቀት በየስድስት ወሩ አዘጋጅቶ ለአባሎችና ለሚመለከታቸው ያደርሳል፤በማህበሩ ዓመታዊ በዓላትም ላይ ለሚገኙ ያደርሳል፤

24-6 ለስራው የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶችና በጀቶች ያቀርባል፤ያጠናል፤ሲፈቀድለት በስራ ላይ ያውላል፤

24-7 በማህበሩ ጉዳዮች ላይ የሚመለከታቸውን ሃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ ለአባላት መረጃዎችን ይሰጣል፤

24-8 ከአባላት በፈቃደኝነት አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎችን ይመርጣል፤ ፕሬዝዳንቱ ሲፈቅድለት ተግባራዊ ያደርጋል፤

24-9 ማንኛውም የጽሁፍ፤የኤሌክትሮኒክስ፤የቃለ መጠይቅ መግለጫዎች ሁሉ ከመተላለፋቸው በፊት በፕሬዝዳንቱ መፈቀድ አለባቸው።ለመፈቀዱም የጽሁፍ ማስረጃ ይይዛል፤

24-10 ከኮሚቴዎች ጋር ተባብሮ ይሰራል።

## አንቀጽ 25 ሴቶች ወጣቶችና ህጻናት

25-1 በጾታቸው የሚደርሱ ችግሮችን ለመቅረፍና ለማስወገድ ይሰራል፤

25-2 በማህበሩ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያበረታታል፤

25-3 ባህላቸውን አክባሪ፤ቤተሰባቸውንና ወገናቸውን አፍቃሪ እንዲሆኑ የማበረታቻ የኪነ ጥበብ ዝግጅቶችን ያቀናብራል፤

25-4 ከህዝብ ግንኙነትና ባህል ኪነ ጥበብ ስነ ጽሑፍ ኮሚቴ ጋር በመመካከር ዕቅዶችን ያወጣል፤ያስፈጽማል፤

25-5 በችሎታቸው አርአያ የሆኑትን መርጦ ልምዳቸውን ለሌሎች እንዲያካፍሉ ያመቻቻል፤ ሽልማት እንዲያገኙ ይጥራል።

## አንቀጽ 26 ባህል ኪነ ጥበብና ስነ ጽሑፍ

**26-1 አባላት የፈጠራ ችሎታቸውን በመጠቀም የአገራችንን የተለያዩ ባህሎችና ታሪኮች፤ስነ ጽሑፍ ፤ግጥም፤በስዕል በድራማ፤በሙዚቃ ወዘተ እንዲያቀርቡ ያደራጃል፤ካስፈለገም ያወዳድራል ፤እንዲሸለሙም ያደርጋል፤**

**26-2 የኢትዮጵያ ፊደላትና ቁጥሮች በአባላትና በልጆቻቸው እንዲታወቁ ይጥራል፤ በተወከለበት ስራ ላይም ተግባራዊ በማድረግ እየተረሳ ያለውን ቁጥሮቻችን የመታደግ ሃላፊነትን ይወጣል፤**

**26-3 እንዳስፈላጊነቱ የኢትዮጵያ ምሽት የተሰኘ ፕሮግራም ያዘጋጃል፤**

**26-4 በማህበሩ ዓመታዊ በዓላት ላይ ኢትዮጵያን ለዓለም ያስተዋወቋትን ቅርሶች በመሰብሰብ፤በፊልምና በድምጽ በማቅረብ ያስተዋውቃል፤**

**26-5 በአየርላንድ በሚደረጉ ዓመታዊ የባህል ቀን ከሴቶች ወጣቶችና ህጻናትና ከህዝብ ግንኙነት ኮሚቴዎች ጋር ተባብሮ ማህበሩ እንዲሳተፍ ያደርጋል፤**

**26-6 የአገራችንን ዋና ዋና በዓላት በህብረት የሚዘጋጅበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ያቅዳል።**

## <u>አንቀጽ 27 የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ</u>

**27-1 በምርጫው ቀን በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጡ ሶስት አባላት ይኖሩታል፤**

**27-2 ለምርጫ ኮሚቴ አባልነት የሚመረጡ አባላት ቢያንስ ለሁለት ዓመት አባል የነበሩና የማህበሩን ህጎች ጠንቅቀው የተረዱ መሆን አለባቸው፤**

**27-3 ምርጫ ለማካሄድ ምልዓተ ጉባኤ መሟላት ይኖርበታል፤**

**27-4 ምልዓተ ጉባኤ በመጀመሪያው ስብሰባ ላይ ካልተገኘ በሁለተኛው ስብሰባ በእለቱ ከተገኙት ከ75% በላይ ስብሰባ እንዲቀጥል ከተስማሙ ምርጫው እንዲካሄድ ያደርጋል፤**

**27-5 በምርጫው ወቅት ለጉባዔው የኮሚቴዎችንና የተመራጮችን ሃላፊነት በተመለከተ በቂ ማብራሪያ በመስጠት ምርጫው ግልጽ እንዲሆን ያደርጋል፤**

**27-6 ለእያንዳንዱ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የምርጫ ቦታ ቢያንስ 2 ሰዎች ለውድድር መቅረብ አለባቸው።የተጠቆሙት ሰዎች ለቦታው ብቁ መሆናቸውን ከልብ በሆነ ሃቀኝነት ያረጋግጣል፤**

**27-7 የእጩዎችን ዝርዝር ካሳወቀ በኋላ ምርጫው በግልጽ ድምጽ አሰጣጥ እንዲካሄድ ያደርጋል፤**

**27 -8 አስመራጭ ኮሚቴ ምርጫው በትክክል መካሄዱንና የሁሉም ድምጽ በደንብ መቆጠሩን የምርጫውም ውጤት ለአባሎች መገለጹን ያረጋግጣል፤**

27-9 የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴው የተመረጡት አባላት ለተመረጡበት ዓላማ ቃል መግባታቸውን ያረጋግጣል፤

27 10 የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ሃላፊነት በዕለቱ ያበቃል።

## አንቀጽ 28 አስተያየትና ቅሬታን ስለመግለጽ

28-1 ማንኛውም አባል በተናጠል ወይም ከሌሎች አባላቶች ጋር በጋራ በመሆን የማህበሩንና ቦርድ የስራ አፈጻጸም በተመለከተ ቅሬታ ወይም አስተያየት ሲኖረው ወይም የማህበሩን የስራ አስፈጻሚ የተጣለባቸውን ሃላፊነት በብቃት አልተወጡም ብሎ ሲያምን ቅሬታውን ለቦርዱ በጽሑፍ የማቅረብ መብት አለው፤የደብዳቤውን ግልባጭም ለስራ አስፈጻሚው ይሰጣል፤

28-2 አንድ አባል ወይም ከዚያ በላይ ተመራጮች ከአገልግሎት ቦታቸው መነሳት አለባቸው ብሎ ሲያምን የአባላቱን 30% የድጋፍ ፊርማ በማሰባሰብ ጥያቄውን በጽሑፍ ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል።ቦርዱም የቀረበለትን ጥያቄ መርምሮ በቂ ምክንያት አለ ብሎ ሲያምን ጉዳዩን ከአማራጭ አስተያየት ጋር ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል።እስከዚያም ድረስ እንዳስፈላጊነቱ ጊዜያዊ ውሳኔ ሊያሳልፍ ይችላል።

## አንቀጽ 29 የማህበሩን ህግና ደንብ ስለ ማሻሻል

29 -1 የማህበረሰቡ ቦርድ ማሻሻያዎችን እያጠና ለጠቅላላ ጉባዔው ሲያቀርብና ጠቅላላ ጉባዔው ሲያምንበት ብቻ የማህበረሰቡ ህግና ደንብ ይሻሻላል።የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውና ሌሎች ኮሚቴዎች ማሻሻያዎችን በቦርዱ በኩል ማቅረብ ይችላሉ።በተጨማሪም ማንኛውም አባል ከሌሎች አስር አባላት ጋር በጋራ በመሆን ማሻሻያዎችን በቦርዱ በኩል ማቅረብ ይችላል። ውሳኔውም በቦርዱ በኩል ይፈጸማል።

## አንቀጽ 30 ኃላፊነትና ተጠያቂነት

30-1 በማህበሩ የስራ ድርሻ የሚከናወነው በፈቃደኝነት ቢሆንም በኃላፊነት የተመደቡ ተመራጮች የማህበሩን ህግና ደንብ እንዲሁም በአየርላንድ የማህበሩን ህግን ተከትለው የማህበሩን አንድነት በመጠበቅ የመስራት ኃላፊነትና አደራ የተጣለባቸው ሲሆን ተመራጮች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በተናጠልም ሆነ በጋራ ለሚያደርሱት ጥፋትና ጉዳት ተጠያቂዎች ናቸው፤

30-2 አንድ አባል ወይም ተመራጭ የማህበሩን ስራ እያካሄደ ባለበት ወቅት ለሚያደርሰው ጥፋትና ጉዳት በህግ ተጠያቂ ቢሆን ማህበሩ ሃላፊነት አይወስድም፤ ሆኖም ማህበሩ እንደ አስፈላጊነቱ የበጎ ፈቃድ ርዳታ ሊያደርግለት ይችላል።

## አንቀጽ 31 አበልና ሌላ ክፍያ

31-1 የማህበሩን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በማንኛውም ኮሚቴ ውስጥ የሚያገለግሉ አባላት ምንም ዓይነት ደመወዝ ወይም ክፍያ ሊጠይቁ አይችሉም።ሆኖም ግን ከማህበሩ የስራ

እንቅስቃሴ የተነሳ ከከተማ ውጪ ለሚደረጉ የጉዞና ሌሎች ወጪዎች እንዳስፈላጊነቱ ቦርዱ በሚያጸድቀው የወጭ መጠን መሰረት ወጭ ይደረጋል።ከደብሊን ውጪ የሚደረጉ ጉዞዎች በቦርዱ መጽደቅ አለባቸው፤

31-2 በደብሊን ውስጥ ለሚደረጉ ጉዞዎችና ሌሎች ጊዜያዊና ጥቃቅን ወጪዎች የስራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ፕሬዝዳንት በሚያዘው መሰረት ወጪ ይደረጋል። ጥቃቅን ወጪዎች የስራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ፕሬዝዳንቱ እንግዶችን ለመቀበል ወይም እንዳስፈላጊነቱ መጠነኛ ግብዣ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ወጪዎች ይጨምራል።

## አንቀጽ 32 ማህበሩን ስለ ማፍረስ

32-1 በአንድ ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች የማህበሩ ህልውና አስፈላጊ ከማይሆንበት ደረጃ ሲደርስ በአየርላንድ የማህበሩ ህግ መሰረትና ከጠቅላላው አባላት ቢያንስ 75% የሚሆኑት በሚገኙበት ከጠቅላላ ጉባዔው በሚተላለፍ ውሳኔ መሰረት ማህበረሰቡ ይፈርሳል፤

32-2 በንዑስ አንቀጽ 31 1 ማህበሩ ሲፈርስ የማህበሩ ገንዘብ፤ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ንብረት ጉባዔው ለሚመርጠው በጎ አድራጎት ድርጅቶች ይከፋፈላል።

## አንቀጽ 33 መተዳደሪያ ደንብ የሚጸናበት ጊዜ

33-1 ይህ መተዳደሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባኤ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።